# የኢሚግሬሽን ፖሊሲዎች በ IRC ደንበኞች ላይ ስለሚኖረው ተጽኖ በአብዛኛው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

በጃንዋሪ 20:2025 ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ የኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያና ከስደተኛ መጨመር ጋር የሚያያዙ ተከታታይ የስራ አፈጻጸም ትዛዞችን/መመሪያ አውጥተዋል ። መመሪይው` ከዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንት ፤የተጻፈ ፤ የተፈረመ እና የታተመ ነው። ይህም እንደሌሎች ህጎች ተፈጻሚነቱ ተመሳሳይ ነው። የፌደራል ኤጀንሲዎች የተወሰኑትን እነዚህን ትዛዞች ተግባራዊ ለማድረግ ተጨማሪ መመሪያ አውጥተዋል።

እያንዳንዱ ሰው የተሰደደበት ጉዳይ የተለያየ ነው ።ስለዚህ የርስወን ጉድይ የሚመለከት የኢሚግሬሽን ጠበቃ ወይም የፍትህ ዲፓርትሜንት እውቅና ያለው የህግ ተወካይ እንዲያነጋግሩ ይመከራሉ ።የኢሚግሬሽን ጉዳይ በአዲሱ የአሜሪካ መንግስት እንዴት እንደሚነካዎ ለማወቅ እርግጠኛ መሆን አይቻልምና።

**IRC በዩኤስ ውስጥ ላሉ ደንበኞች ግብኣቶችን ፈጥሯል ።ይህም ሰዎች መብታቸውን እና የኢሚግሬሽን ሂደቱን በደንብ እንዲረዱ እንደሚረዳቸው ተስፋ እናደርጋለን።ነገር ግን ይህ መረጃ ብቃት ካለው ጠበቃ ወይም የህግ እውቅና ካለው የህግ ተወካይ ምክርን የሚተካ አይደለም።**

**ማስታወሻ ፤** የቀረበው መረጃ ከጃንዋሪ 24፤2025 ጀምሮ ትክክለኛ ነው።እና በበለጠ የፖሊሲ ለውጦች /ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔዎች ምክንያት በፍጥነት ሊለወጥ ይችላል።



## አዲሱ የኢሚግሬሽን ፖሊሲ እንዴት ይመለከተኛል?

**እኔ ህጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ አለኝ (ግሪን ካርድ ማስረጃም ተብሎ ይጠራል)። በነዚህ አዳዲስ ፖሊሲዎች መሰረት መረጃየን የማጣት/መቀማት ወይም የመባረር ስጋት አለብኝ ወይ?**

**አይደሉም ።** እንደ ቋሚ ነዋሪ በዩናይትድ ስቴትስ ለመኖርና ለመስራት ላልተወሰነ ጊዜ ፈቃድ አለወት ።ማጭበርበር ካልፈጸሙ ፤ ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ ለረጅም ጊዜ በመቆየት የመኖሪያ ቦታዎን ካልተው፤ ወይም የተወሰኑ የወንጀል ጥፋቶችን እስካልፈጸሙ ድረስ የመባረር ስጋት ሊገባዎት አይገባም።ከነዚህ ውስጥ አንዳቸውም ይመለከተኛል ብለው ካመኑ ፤ ስጋትዎትን ለመገምገም የኢሚግሬሽን ጠበቃ ወይም የፍትህ ዲፓርትሜንት (DOJ) እውቅና ያለው የህግ ተወካይ ማነጋገር አለበወት። ለዜግነት ማመልከቻ ከማቅረብ በፊት ቋሚ ነዋሪዎች ከኢሚግሬሽን ጠበቃ ወይም እውቅና ካለው ተወካይ ጋር እንዲነጋሩ ይበረታታሉ።

ህጋዊ ቋሚ ነዋሪነተዎን (LPR) ካለዎትና በህግ አስከባሪዎች ከተጠየቁ እርስዎ ቋሚ ነዋሪ መሆንዎን ያሳውቋቸው እና የ LPR ካርድዎን ያሳዩአቸው።

**እኔ ያፍጋኒስታን ወይም የኢራቅ ልዩ ስደተኛ (SIV) ነኝ። በእነዚህ አዳዲስ ፖሊሲዎች ህጋዊነቴን የማጣት ወይም የመባረር አደጋ አለብኝ ወይ?**

**አይደሉም ።** በልዩ የስደተኛ ቪዛ (SIV) ወደ አሜሪካ የገቡ ውይም በተፈቀደ የ (SIV) አቤቱታ ወይም ተለእኮ ዋና ፈቃድ ላይ ተመስርተው የደረጃ ማስተካከያ የተሰጣቸው ቀድሞውንም ህጋዊ ቋሚ ነዋሪዎች ናቸው።

በኢራቅ ወይም አፍጋኒስታን ውስጥ ላለው የአሜሪካ ተልዕኮ ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት አገልግሎት ላይ በመመስረት እንደ ልዩ ስደተኛ ለመመደብ ያቀረቡትን ጥያቄ ዋና ኦፍ ሚሲዮን (COM) ፈቃድ ጠይቀው ነገር ግን እስካሁን ያልደረሰዎት ከሆነ እስካሁን ድረስ በህጋዊ መንገድ አይደሉም። ለሌላ ጊዜያዊ ወይም ዘላቂ እፎይታ መንደ ጊዜያዊ ጥበቃ ሁኔታ ወይም ጥገኝነት ብቁ መሆንዎን ለማየት የህግ አገልግሎት ሰጪን ማማከር አለብዎት ።

LPR ከሆንክ ወይም ሌላ ህጋዊ አቋም ከያዝክ ሁል ጊዜ ህጋዊ መሆንህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ መያዝ አለብህ ። COM ተቀባይነት ካለወት እና ለሁኔታ ማስተካከል ካስገቡ ከUSCIS (1-797) የ1-484 ደረሰኝ ሁልጊዜ ከእርስዎ ጋር ይዘው መሄድ አለበዎት።

**ማስታወሻ :** በመጠባበቅ ላይ ያለ የደረጃ ማመልከቻ መኖሩ እርስዎን ከመታሰር ወይም ከመባረር አይጠብቅዎትም ወይም አያድንዎትም።

**እኔ ጥገኛ ወይም ስደተኛ ነኝ። በእነዚህ አዳዲስ ፖሊሲዎች መሰረት የስደተኛን ከለላየን የማጣት ወይም የመባረር ስጋት አለብኝ ወይ?**

## አይደሉም ።

እንደ ጥገኝነት ወይም ስደተኛ በዩናይትድ ስቴትስ ላልተወሰነ ጊዜ ከለላ/ጥበቃ ተሰጥቶዎታል። የማጭበርበር /የማታለል ድርጊት ካልፈጸሙ ፤ ወደ ትውልድ ሃገርዎ ካልተመለሱ ወይም የተወሰኑ የወንጀል ጥፋቶችን እስካልፈጸሙ ድረስ ወደ መባረር ውይም መፈናቀል ሂደት ውስጥ ሊገቡ አይችሉም ። (ክነዚህ ውስጥ አንዱ እርስዎን የሚመለከት ከሆነ ፤ የእርስዎን ስጋቶች ለመገምገም የኢሚግሬሽን ጠበቃ ወይም የ DOJ እውቅና ያለው የህግ ተወክይ ማነጋገር አለብዎ) ። **ጥገኝነት ጠያቂዎች / ስደተኞች በዩኤስ ውስጥ የአንድ አመት ቆይታቸውን ሲያጠናቅቁ በተቻለ ፍጥነት ከኢሚግሬሽን ጠበቃ ወይም እውቅና ካለው ተወካይ እርዳታ መጠየቅ አለባቸው።**

ምንጊዜም የጥገኝነት ወይም የስደተኝነት ሁኔታዎን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይዘው መሄድ አለብዎት። የህግ አስከባሪ አካላት ካስቆመዎና ስለ ስደተኝነት ሁኔታዎ ከተጠየቁ የጥገኝነት ማስረጃዎን እና ወይም (ሀ)(5) የስራ ፈቃድ ወይም የስደተኛ ማስረጃ (የስደተኛ ሰነድ የመግቢያ ማረጋገጫ ) ማሳየት አለብዎት ። ወይም (ሀ) (3) የስራ ፈቃድ ማስረጃ ማሳየት አለብዎት ።

**ጊዜያዊ የከለላ/መቆያ ማስረጃ TPS (TPS) አለኝ ። በነዚህ አዳዲስ ፖሊሲዎች መሰረት ከለላዬን የማጣት ወይም የመባረር አደጋ አለብኝ ወይ?**

## ምናልባት/አጠራጣሪ ነው

በህግ ፕሬዚዳንቱ ሁሉንም የTPS አገሮች ፈቃዱ ከማለቁ በፊት እነማን እንደሆኑ መገምገምና ማራዘም ወይም ማቋረጥ እንደሚገባቸው መወሰን አለባቸው። **TPS ከተቋረጠ፤ በአሁኑ ጊዜ TPS ያላቸው TPS ወይም የስራ ፈቃዳቸውን ማደስ አይችሉም እና ሊታሰሩ እና /ወይም ሊወገዱ ይችላሉ።** ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ፤ የTPS ምንም መቋረጦች እስካሁን የሉም።

የ TPS ሁኔታዎን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሁልጊዜ ይዘው መሄድ አለብዎት። በሕግ አስከባሪ አካላት ከቆሙ እና የኢሚግሬሽን ሁኔታዎን ከተጠየቁ የ TPS ማጽደቂያ ማስታወቂያዎን/ማስረጃዎን እና ወይም (a) (12) ወይም (c) (19) የስራ ፈዋድዎን ማሳየት አለበዎት።

**የሰባዊ መብት (Parolee) ማስረጃ አለኝ ። በነዚህ አዳዲስ ፖሊሲዎች መሰረት ከለለዬን/ጥበቃዬን የማጣት ወይም የመባረር አደጋ ላይ ነኝ ወይ?**

## ትክክል/አዎ ።

**ፕሬዚዳንቱ ለስደተኞች የምህረት አዋጅን ሊሰርዙ ይችላሉ ፣** እና በቅርብ ጊዜ በፖሊሲው ላይ የተደረጉ፤

- ፕሬዚዳንቱ ለማቋረጥ የሚቻሉትን ሁሉንም የይቅርታ ፕሮግራሞች እየገመገሙ ነው።
- አዲስ ህግጋቶች በአፋጥኝ ስደተኞች እንዲታሰሩና እንዲባረሩ ሊፈቀድ ይችላል።
- የአሁኑ ጊዜ ካለቀ በኋላ እንደገና ይቅርታ ማድረግ አይቻልም። *እባክዎን ለCHNV ዳግም ይቅርታ የለም። (CHNV የኩባ፤ የሄይቲ ፤ የኒካራጓ እና የቬንዙዌላ የይቅርታ ፕሮግራም የለም) ።

የተለያዩ የህግ አማራጮችን እና ከሃገር መባረርን ለመከላከል እንዲያስችል **ከኢሚግሬሽን ጠበቃ ወይም እውቅና ካለው ተወካይ ጋር ባስቸኳ ማማከር** አለባቸው ።

## የጉዞ ምክሮች፤ ህጋዊ ላልሆኑ ቋሚ ነዋሪዎች ወይም የአሜሪካ ዜጎች (በተጨማሪ አሲሊዎች/ASYLEES፣ ስደተኞች፣ የTPS ያዥዎች/holders እና Parolees ንም ጨምሮ)

የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት በአሁኑ ጊዜ የጉዞ እገዳዎችን እየገመገመ ስለሆነ፣ እስካሁን ድረስ ህጋዊ ቋሚ ፈቃድ (ግሪን ካርድ) ያላገኙ ግለሰቦች የጉዞ እገዳ እንደሚወጣ እና ለዚያም የበለጠ ግልፅ እስካልሆኑ ድረስ ከዩናይትድ ስቴትስ እንዳይወጡ **በጥብቅ ይመከራል።** አገሮች፣ ወይም የLPR ሁኔታዎን (ግሪን ካርድ) እስኪያገኙ ድረስ ፤ ከሜክሲኮ ወይም ካናዳ ድንበር በ100 ማይል ርቀት ላይ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የኢሚግሬሽን ኬላዎች እንዳሉ እባክዎን ያሳውቁ። በአገር ውስጥ የሚጓዙ ከሆነ ወደነዚህ አካባቢዎች ከመጓዝ ይቆጠቡ።



# ከእኔ ጋር ምን ምን ሰነዶችን መያዝ አለብኝ?

**ማስታወሻ/ማሳሰቢያ፤** በማንኛውም ጊዜ ኦርጅናል// ዋናውን ሰነዶችን ወይም የወረቀት ቅጂዎች እንዳለዎት ያረጋግጡ ። በቤት ውስጥ ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ተጨማሪ ቅጂዎች እንዳሉዎት ያረጋግጡ።

| ሁኔታ | የሚያዙ ሰነዶች |
| --- | --- |
| **አሁን ያለው የኢሚግሬሽን ሁኔታ** ካለዎት | በዩኤስ ውስጥ ያለዎትን የኢሚግሬሽን ሁኔታ የሚያረጋግጥ ሰነድ ሁልጊዜ ይያዙ፣ ለምሳሌ፤<br><br>1. **I-551** ህጋዊ የቋሚ መኖሪያነት ማረጋገጫ (ግሪን ካርድ)<br>2. **I-94** ህጋዊ የመግባት ወይም ማህተም ያለበት ፓስፖርት ወይም ሌላ የጉዞ ሰነድ ከቪዛ/የመግቢያ ማህተም ጋር<br>3. **የሥራ ፈቃድ ካርድ** (የሥራ ፈቃድ)<br>4. **I-797** የማጽደቂያ ማስታወቂያ ለስደት ሁኔታዎ<br>5. **በግዛት/በስቴትቶች የተሰጠ መንጃ ፍቃድ** — መንጃ ፍቃድ ለማግኘት የእርስዎ ግዛት አሁን ያለውን የስደት ሁኔታ የሚፈልግ ከሆነ ብቻ ነው። |
| **ሁኔታዎ በመጠባበቅ ላይ ከሆነ** (ይህ ማለት ለኢሚግሬሽን ጥቅም ወይም ጥበቃ አመልክተዋል ነገር ግን በእርስዎ ጉዳይ ላይ እስካሁን ምንም ውጤት አያገኙም) | **ከUSCIS (I-797)** የደረሰኝ ቅጂ በማንኛውም ጊዜ ከእርስዎ ጋር እንዳይለየዎት ።<br><br>**ማስታወሻ :** በመጠባበቅ ላይ ያለ የደረጃ ማመልከቻ መኖሩ እርስዎን ከመታሰር ወይም ከመባረር አያድንዎትም። |
| **ለመባረር በሚያስችል ሂደት እና የስራ ፍቃድ ማስረጃ ከሌለዎት** | ላስገቧቸው ማንኛውንም **ደረሰኝ ወይም የይቅርታ ማስታወቂያ /parole notice** (እርስዎን የሚመለክከትዎ ከሆነ) የእርስዎ ቀጠሮ **የሚሰማበት ማስታወቂያ** ግልባጭ ይያዙ ። |
| **ሰነድ አልባ** ከሆኑ | የሀገረወን የብሔራዊ መታወቂያዎን ወይም ፓስፖርትዎን **ቅጂ እንዳይዙ ምክንያቱም እነሱ በኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት ሊጠቀሙበት ይችላሉ።**<br><br>**ማሳሰቢያ :** የሌላ ሰው ንብረት የሆነ ማንኛውንም የውሸት ሰነድ ወይም ሰነድ መያዝ የለብዎትም። |
| **ሰነድ ከሌለዎት** ወይም **ሁኔታዎ በመጠባበቅ ላይ** ከሆነ ፣ እርስዎ **የማስወገድ ሂደት ላይ አይደሉም፣ እና ለ 2 ዓመታት ወይም ከዚያ በላይ በአሜሪካ ውስጥ ነበሩ** | እራስዎን ከተፋጠነ መወገድ ለመጠበቅ በUS ውስጥ ለ2+ ዓመታት **የአካል መገኘትዎን የሚያረጋግጥ ማስረጃ** ይያዙ ።<br><br>**ማስታወሻ :** ይህ እርስዎን ከመታሰር ወይም ከመባረር ሙሉ በሙሉ አይከላከልልዎትም/አያድንዎትም ነገር ግን ከተፋጠነ መባረር/መወገድ ሊጠብቅዎት ይችላል።<br><br>ይህ የሚከተሉትን ቅጂዎች ሊያካትት ይችላል:-<br>• ላለፉት ሶስት አመታት ግብር የማስገባት (ይህ የሚሰራው ግን ITIN ወይም የሶሻል ሴኩሪቲ # ስራ ላይ ከዋለ ብቻ ነው)<br>• ቤት የተክራዩበት ሰነዶች<br>• የፍጆታ (ለምሳሌ የውሃ፤ የመብራት የመሳሰሉት ክፍያ)<br>• የእርስዎ ወይም የልጆችዎ ትምህርት ቤት ማስረጃዎ<br>• በዩኤስ ውስጥ ከሁለት አመት በላይ እንደቆዩ የሚያረጋግጡ ሰነዶች ሊኖሩዎት ይገባል። |



# መብትዎትን ይወቁ!

በዩናይትድ ስቴትስ የሚኖሩ ሁሉም ሰዎች፣ የስደት ሁኔታቸው ምንም ይሁን ምን፣ በዩኤስ ሕገ መንግሥት የተወሰኑ መሠረታዊ መብቶች አሏቸው። ጊዜያዊ የስደት ሁኔታ ያላቸው ሰዎችም እነዚህ መብቶች አሏቸው። መብትዎን ይወቁና ከፖሊስ ጋር ወይም ከኢሚግሬሽ እና ጉምሩክ አስተባባሪ (አይሲኢ) መኮነኖች ጋር በሚገናኙበት ጊዜ እነሱን ለመጠቀም አይፍሩ።

**በፖሊስ ወይም በኢሚግሬሽን መኮንን ካቆሙ ወይም ከተጠየቁ፣**
**የሚከተሉት መብቶች እንዳለዎት ያስታውሱ።**

- **ከነርሱ ጋር ለመነጋገር እምቢ ማለት ይችላሉ .** እንደተወለዱ ወይም እንዴት ወደ አሜሪካ እንደገቡ መናገር አይጠበቅብዎትም።
- የዩኤስ ዜጋ ካልሆኑ እና የኢሚግሬሽን መኮነን ወረቀትዎን ከጠየቁ፤ እና ከያዙ ማሳየት አለበዎት ።የኢሚግሬሽን ሰነዶችን በማንኛውም ጊዜ ከእርስዎ ጋር ይዘው ይሂዱ ። **የኢሚግሬሽን ወረቀቶች ከሌሉዎት ዝም ማለት እንደሚፈልጉ ይናገሩ።**
- **ከጠበቃ ጋር የመነጋገር መብት አለዎት።**
- **ማንኛውንም ነገር ከመፈረምዎ በፊት ጠበቃን ያነጋግሩ።**
- በቋንቋህ የተተረጎመ **የመብቶችህን የማወቅ ካርድ ይዘህ** የኢሚግሬሽን መኮንን ካቆመህ አሳይ። (ከዚህ በታች ተጨማሪ የQR ምንጮችን ይመልከቱ)።

**መብቶችህን እንዴት ማስጠበቅ እንደምትችል ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከታች ያሉትን ማገናኛዎች ይቻላል።**

**ILRC Red Cards**

ILRC.ORG/RED-CARDS-TARJETAS-ROJAS

**We Have Rights (ቪዲዮዎች እና ቁሳቁሶች)**

WEHAVERIGHTS.US

# እንዴት እርዳታ ማግኘት እችላለሁ?

**ግሪን ካርድ ወይም የአሜሪካ ዜግነት አለህ? ካልሆነ፣**
ቋሚ የኢሚግሬሽን ሁኔታ ለማግኘት ስላሎት አማራጮች የኢሚግሬሽን ጠበቃ ወይም የፍትህ ዲፓርትመንት እውቅና ያለው ተወካይ ያነጋግሩ ። የኢሚግሬሽን ጠበቃ ወይም እውቅና ያለው ተወካይ እርስዎ ለቋሚ ደረጃ ብቁ መሆንዎን ይገመግማሉ ። ለቋሚ የስደተኝነት ሁኔታ ብቁ ከሆኑ፣ የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚደንት የሆነው ምንም ይሁን ምን ሁልጊዜ እሱን መከታተል ይመከራል።

## ከኢሚግሬሽን ጉዳይ አጭበርባሪዎች ይጠንቀቁ!

ስለ እሚግሬሽን በቂ እውቀት ያለው የህግ ጠበቃ ወይም DOJ እውቅና የተሰጠው ድጋፍ እንዲሰጥዎ ይጠይቁ።

- ያስታውሱ የኢሚግሬሽን ጠበቆች እና እውቅና ያላቸው ተወካዮች ብቻ የህግ ምክር ሊሰጡዎት ይችላሉ። ከ notarios ይጠንቀቁ ወይም የኢሚግሬሽን ምክር ለመስጠት ስልጣን የሌላቸው ወይም ብቁ ያልሆኑ የህዝብ ማስታወሻዎች። ጊዜዎን እና ገንዘብዎን ያጠፋሉ እና እርስዎን እና ጉዳይዎን ትልቅ አደጋ ላይ ሊጥሉ ይችላሉ።

- በጉዳይዎ ላይ የሚረዳዎትን ሰው ከመቅጠርዎ በፊት ብቃቱን እንዲሰጥዎት ባለሙያውን ይጠይቁ። ግለሰቡ ጠበቃ ነው ወይስ እውቅና ያለው ተወካይ? ግለሰቡ በኢሚግሬሽን ህግ ምን ያህል ልምድ አለው? ስለ ኢሚግሬሽን ማጭበርበሮች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ይህን ሊንክ ይጫኑ ። እንዲሁም ዝቅተኛ ወይም ምንም ወጪ ሊረዳ የሚችል የተፈቀደ የህግ አገልግሎት አቅራቢ ለማግኘት ይህንን ማውጫ ይመልከቱ (እንዲሁም ከዚህ በታች የQR ኮድ ይመልከቱ)።

**በከተማዎ ውስጥ ነፃ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ያለው የህግ ድጋፍ ለማግኘት ከታች ያሉትን ማገናኛ ይጠቀሙ ፦**

ነፃ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ያለው የሕግ ድጋፍ ለማግኘት የሚረዳ ብሔራዊ የሕግ ማውጫ

**Immigration Advocates Network**

IMMIGRATIONADVOCATES.ORG/LEGALDIRECTORY/

ያለ ወላጅ ወይም ህጋዊ አሳዳጊ ወደ አሜሪካ ለገቡ ወጣቶች

**ImportaMí**

IMPORTAMI.ORG/EN-US